# ለእግዚአብሔር ፍቅር

> ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡
> (ኢሳ 54÷13)

የካቲት 1994 February 2002

# መስጠትና




# . . . መቀበል

መስጠት የዕምነት ውጤት ነው፡፡ ሰው ከልቡ ለሚወደው ነገር ገንዘቡን ያወጣል፡፡ ገንዘቡን በታማኝነት የሚያወጣበት ነገር በሰውየው ሕይወት ውስጥ ተቀዳሚ ሥፍራ አለው፡፡ እግዚአብሔር በሕይወቱ ተቀዳሚ ሥፍራ የያዘለት ሰው ደግሞ እንደዚሁ ነው፡፡ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር የተማረና ሁሌም የሚማር ይሆናል፡፡ ስለሆነም መስጠትንና አሥራትን የመሳሰሉትን አስመልክቶ መደረግ ያለበትን ያውቃል፡፡

እግዚአብሔር ሲባርክ አሠራሩ አስገራሚ ነው፡፡ የሚሰጥ ይቀበላል፡፡ ብዙ ለሚሰጥ ደግሞ ይበዛለታል፡፡ ለሚሰጥ ሰው ተመልሶ የሚሰጠው ዓይነት በዓይነት ላይሆን ይችላል፡፡ ለግዚአብሔር ሥራ የሚሰጥ ሁሉ ግን በምንም ዋጋ ሊተመን የማይችል መንፈሳዊ በረከት ይቀበላል፡፡ ይህንንም ስንል ቁሳዊ በረከት አይቀበልም ማለት ሳይሆን በምድራዊው ነገር የታመነውን ያህል በሰማያዊውም ስለሚታመን፡ ከመልካም ነገር ሁሉ አይከለከልም ለማለት ነው፡፡ በምድራዊው ያልታመነ በሰማያዊው ሊታመን እንዴት ይችላል ?

በቸርነት እግዚአብሔር ሁሉን ይበልጣል፡፡ ለሰውም መልካም የሆነውን ሁሉ መስጠት ይፈልጋል፡፡ በእግዚአብሔርም ዘንድ እንደ ሰው ልጅ የተወደደ ፍጥረት የለም፡፡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ለሰው ልጅ ደኅንነት አንድያ ልጁን አሳልፎ መስጠቱ ነው፡፡ ራሱ ታላቅ ስጦታ በመስጠት አርአያ የሆነው ጌታ የመቀበል መንገዱ መስጠት መሆኑን ሲያስተምረን እንዲህ ይላል ፡-

"<u>ስጡ ይሰጣችሁማል</u>፡በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፡<u>የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል</u>፡፡" ይላል ፡፡ (የሉቃስ ወንጌል 6÷38) ለመሆኑ ክርስቲያናዊ መስጠት እንዴት ነው?

* **የፍሬን በኩራት መስጠት** ፡- "እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር ÷ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት፡" (መጽሐፈ ምሳሌ 3÷9)

* **ተመጣጣኝ መስጠት** (proportional) ፡- ለእግዚአብሔር ሥራ የምትሰጠው አሥራት በገቢህ መጠን መሆን ይገባዋል፡፡ ለምሳሌ ከአሥር ብር አንድ÷ ከመቶ ብር አሥር÷ ከሺህ ብር መቶ ብር ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ከሺህ ብር መቶ የሚሰጠውንና ከአሥር አንድ የሚሰጠውን በእኩልነት ይመለከታል፡፡ ሺ ብር እያገባ አንድ ብር የሚሰጠው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ታማኝ ሊቆጠር አይችልም፡፡ ተመጣጣኝ አሰጣጥ ለሐብታሙም ለድህውም እኩልነት ነው፡፡ (1ቆሮ 16÷3)

* **የመስዋዕት መስጠት** (sacrificiall) ፡- አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከጉድለታችን እንድንሰጥ ይፈልጋል ፡፡ ሳይተርፍ ከራስ አጎድሎ ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡ የምፈልጉትን ነገሮች ትቶ ወይም ለሌላ ጊዜ አስተላልፎ መስጠት ÷ ለመስጠት ሲሉ አኗኗርን መለወጥ ወዘተ፡፡ በመስዋዕትነት ስንሰጥ ስጦታችን የከበረ ስጦታ ይሆናል፡፡ ቃሉ እንዲህ ይላል፡- <u>"በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል</u>፤<u>*እንደ አቅማቸው መጠን ፡ ከአቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና*</u>፡፡ (2 ቆሮ 8÷2-3)

ሌላው ከዚህ ጋር በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት ጥሩ ምሳሌ፡- ነቢዩ ኤልያስን ትመግብ ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛትን ባልቴት ታሪክ ነው፡፡ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17÷ 8-16 እንደተጻፈው (አንብቡት) "ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዥዣለሁ" (ቁ 9) በማለት ለኤልያስ

ሲናገር እንመለከታለን። በዚያው ክፍል የባልቴቲቱን ኢኮኖሚ ሁኔታ ከራሷ ምስክርነት እናገኛለን። በዚህ ዘመን ሥራ አጥ እንደሚባል በጣም ድሀ መሆኗን በመሐላ ተናግራለች።(ቁ 12) እግዚአብሔር ግን ነቢዩን እንድትመግብ አዘዛት። ትዕዛዙ ከተፈጸመ በኋላ እግዚአብሔርም ፣ ነቢዩም ፣ ባልቴቲቱም ደስተኞች ሆነዋል። አለመታዘዝ ቢኖር ግን ነቢዩ ከዚያ በፊት እንደነበረው በቁራም ቢሆን መመገቡ አይቀርም። ባልቴቲቱና ልጇ ግን በርሀብ ይሞቱ ነበር። ከበዛው መስጠት ለንፉጎችና ለማይታዘዙት እንኳ ፈተና አይሆንም። ከጐደለው መስጠት ግን የታማኝነት መለኪያ ነው። በአሥራታችን ምን ያህል እንታመናለን?

* **በቋሚነት መስጠት** ፦ መጽሐፍ ቅዱስ “በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን” በማለት፣ ምን ያህል አዘውትረን መስጠት እንዳለብን ያመለክታል። አንዳንድ ጊዜ ኑሮ አይከብድም ማለት አይቻልም ሆኖም አሥራትን አለማውጣት የሚያስከትለው መንፈሳዊ ኪሳራ ለማንም አይበጀውም።(1 ቆሮ 16፣2)

* **በደስታ መስጠት** ፦ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰው መቀበል ደስ ይላል። ማለትም አለበት። መስጠት ግን ከስሜት ሁሉ በላይ የሆነ የነፍስ ሐሴት ይሰጣል። መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሥራና ለሰው በመስጠት መታዘዛችንን በመጠቀም ዕምነታችንን ያበረታል። ያም ደግሞ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥልቅ ወደ ሆነው በረከት የምንገባበት የጽድቅ ጉልበት ይሆነናል። “ይህንን እላለሁ፦ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደገሞ ያጭዳል። <u>እግዚአብሔር በደስታ የሚዘራውን (የሚሰጠውን)</u> ይወዳልና፦...”(2 ቆሮ 9፣6-7)

በመስጠት ያለውን ደስታና ትርፍ አለማወቅ አሳዛኝ ነገር ነው። ዐይናችን ተከፍቶ ብናይ ፣ የስንቶቻችን በረከት በራሳችን ንፍገት ታግዶና ተጠራቅሞ ተቀምጧል?

* **ለታይታ ያልሆነ መስጠት** ፦ ለእግዚአብሔርም ሥራ ሆነ ለሰው ስንሰጥ ዓላማችን እግዚአብሔርን ማስደሰት መሆን አለበት። የሰው ማድነቅ ጊዜያዊ ፣ የእግዚአብሔር ደስታ ግን ዘላለማዊ ዋጋ እንዳለው በማወቅ የራስን ቸርነት አለማወጅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፦ “ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ <u>ተጠንቀቁ</u>፣ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ <u>ዋጋ የላችሁም፡</u> (የማቴዎስ ወንጌል 6፣1)

* **አሥራት መስጠት**፦ “ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብራምም ከሁሉ <u>*አሥራትን*</u> ሰጠው።” (ኦሪት ዘፍጥረት 14 ፣ 20) ይህ ቃል የተፈጠረው፦ <u>አሥር-አት</u> ወይም <u>አሥር-አንድ</u> ከሚሉት የሁለት ቃላት ቅንጅት ነው። ይህም ለአማርኛ ተናጋሪዎች የአሥራትን ስሌት የሚያቃልል ቢሆን መልካም ነው። ምክንያቱም ስውርነት የሌለ ውና ሲነገር እንደምንሰማው <u>*ከአሥር አንድ*</u> ማለት ስለ ሆነ ነው።በእግዚአብሔር አሠራር፣እርሱ ከምድር ፍሬ አሥሩን በአደራ ይሰጠናል። በመጀመሪያ አንዱን መልሰን ለእርሱ እንሰጣለን። እርሱ ደግሞ በመታዘዛችን የተነሣ፣የቀረውን ዘጠኙን ነቀዝ ሆነ ልዩ ልዩ ተባይ እንዳይጋራ ያዝዛል። ለዚህ ነው በአሥራት ያልታመኑ ሰዎች የወጪአቸው ብዛት ሁሌ ከገቢያቸው የሚበልጠው። ለነገሩ ዘጠኝ የማይበቃውን አሥር ይበቃዋል ብሎ ማሰብ ብልህ አስተሳሰብ አይደለም። ስለዚህ በአሥራት ላይ ያለን አመለካከት ዕምነታችን የቱን ያህል ዕውነተኛ መሆኑን ለራሳችን ሊያሳየን የሚገባ መስታወት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ያለውና፣እግዚአብሔርን ከሐብትህ አክብር ከፍሬህም ሁሉ በኩራት፦ ያለው ቃል እኩል የታመነ ፡ ስለ ሆነ ነው። በአሥራት ታማኝ በመሆንና በመታዘዝ ወደተትረፈረፈ በረከት የምትገባበት ዓመት ይሁንልህ። አሜን።

---

**“እግዚአብሔርን ከሐብትህ አክብር፣ከፍሬህም ሁሉ በኩራት”**

•

*መጽሐፈ ምሳሌ 3፣9*

**“ስጡ ይሰጣችሁማል፡ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፡የተጨቆነና የተነቀነቀ፣የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።”**

*የሉቃስ ወንጌል 6፣38*



# ባሕሪይና ትዳር

ትዳርን ስናስብ ብዙ ጥንቃቄና ጥናት እናደርጋለን፡፡ ገና ሀ
ሳቡ በልባችን ካደረበት ጊዜ ጀምረን እንፀልያለን፡፡ "የሚስማማኝን
ሰው/ሴት ስጠኝ" እያልን በፆም ራሳችንን እናደክማለን፡፡ ከዚያም ያ
ሰው/ሴት የተገኘ ሲመስለን÷እግዚአብሔር ማረጋገጫ እንዲያሳየን
እንፀልያለን፡፡ ዳሩ ግን እስከዛሬ ድረስ በምንም የማይጋጩ ባሕሪያት
ያላቸው ባልና ሚስት አልታዩም፡፡ ምክንያቱም በሁሉ አንድ ዓይነት
የሆኑ ሁለት ሰዎች ስላልተፈጠሩ ነው፡፡

ሁለት የተለያየ ባሕሪይ ያላቸው ሰዎች በትዳር ሲጣመሩ÷
የባሕሪያቸው ልዩነት የሚደጋገፍ ወይም የሚጋጭ ይሆናል፡፡ የራሳ
ችንንና የባለቤታችንን ባሕሪይ ተረድተን እንደ ጥሩ ቀማሚ በጥንቃ
ቄ ብናስተባብረው ግን አብረን እግዚአብሔርን የምናስከብር ደስተኛ
ባለትዳር እንሆናለን፡፡ የመቀራረን ሕይወት ሳይሆን አንዱ የሌላኛው
ን ጉድለት ተረድቶ ለመሙላት የሚሞክርበት የመቻቻልና የመረዳዳ
ት ትዳር ይሆናል፡፡

<u>ትዳር ሥራም÷ትምሕርት ቤትም÷ማረፍያ ሥፍራም ነው፡፡</u>
ይህም መሆን ያለበት እስከ ዕለተ ሞት ነው፡፡ ትጉሕ ገበሬ ሳያቋርጥ
የእርሻን ብልሀት እየተማረ÷አረሙን በጊዜው እየነቀለ÷ አዲሱን ዘር
በጊዜው እየዘራ በመከር ጊዜ አርፎ እንደሚበላ፡- ትዳርም እንዲሁ
ነው፡፡ የሚከተሉት ሀሳቦች የባሕሪይን ልዩነት በመረዳት ትዳርን የተ
ሻለ ለማድረግ የሚረዱ ናቸው፡፡ (personality plus for couples ከሚል መጽሐ
ፍ ተወስዶ የተዘጋጀ)

-- የራስህንና የባለቤትህን እውነተኛ ባሕሪይ እንዲገልጽልህ መንፈስ
ቅዱስን ባለማቋረጥ ጠይቅ፡-
-- ባለቤትህ በአስተሳሰብና በተግባር ያንተ ካርቦን ቅጅ ብትሆን ደ
ስተኛ የምትሆን መስሎህ ልትለውጣት አትሞክር ፤ ይልቁን ልዩነቱ
ትዳራችሁን የሚያበለጽግበትን መንገድ ለመረዳት ትጋ፡፡
-- ትዳርህን ብሩክ ለማድረግ አንተ ራስህ መማር ያለብህን ሁሉ
እንዲያሳይህ መንፈስ ቅዱስን ዘወትር ጠይቀው፤ በእግዚአብሔር ፀጋ
ዘወትር ለማደግና ባለቤትህንም በእድገቷ ለመርዳት ውሳኔ አድርግ፡፡
-- መሻትህንና ስጋትህን ዘወትር ለባለቤትህ አጫውት፡፡ የባለቤትህ
ንም ሃሳብና ብሶት በጥሞና ስማ፡፡ ከዚያም አብራችሁ ጸልዩበት፡፡
ሰው ሊያደርገው ወይም ሊሆን የማይችለውን ነገር ከባለቤትህ አትጠ
ብቅ፡፡ ምንም ቢሆን የመጨረሻው ርካታና ሙላትህ እግዚአብሔር
እንጂ ባለቤትህ አንዳልሆነች ተረዳ፡፡
-- በሀሳብ ስትለያዩ ለመደፋፈር ከመፍጠን ይልቅ በትዕግሥት አስ
ታራቂ ሃሳብ ፈልገህ ተስማማ፡፡ ነገር ከከረረ አንተ ተረች ሁን፡፡ ከሁ
ለቱ የሚበረታው ለሰላም ሲል ፈቅዶ ይረታ፡፡
-- ለውሳኔ የሚያስቸግር ነገር ሲያጋጥም መልሱ እስኪመጣ በፀሎት
መቆየት እንጂ በነገሩ ላይ መጣላት ለማንም አይጠቅምም፡፡
-- ፍቅር ለሁሉ ሰው የሚገባው በአንድ መንገድ ስላይደለ ÷ ባለቤ
ትህ በሚገባት መንገድ ፍቅርን ግለጽላት፡፡ ለምሳሌ አንተ ስጦታ ት
ወድ ይሆናል፡፡ ባለቤትህ ግን ከሥራ መልስ አረፍ ብለህ ብታጫው
ታት ደስታውን አትችለውም ይሆናል፡፡ እወቅበት!!
-- የቤታችሁን ኃላፊነት በአንዳችሁ ላይ ጫና በማይሆንበት ሁኔታ
ተካፈሉት፡፡
-- ማንም ሳያቋርጣችሁ አብራችሁ ጊዜ የምታሳልፉበትን ሁኔታ
በቋሚነት ይኑራችሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ግጭት ሊያነሣሣ ከሚችል ........

...ማንኛውም ዓይነት ጨዋታ (ንግግር) ራቅ፡፡ ከዚያ ይልቅ
ሁን ብለህ ደስታ ያለበትን÷ሳቅ ያለበትን÷ጭውውት ፈልግ፡፡

በመጨረሻም፡- ፍጹም የሆነ ትዳር አለመኖሩን ዕወ
ቅ፡፡ በሰላም የሚኖሩ ባለትዳሮች በጎረቤትህ ቢኖሩ፡- ስለሚ
ቻቻሉ ብቻ ነው፡፡ ሰላምና ደስታን ከሴይጣን መንጋጋ መን
ጭቆ ለማውጣት የሚችል እንደ መቻቻል ያለ ብርቱ ሽብል
ቅ አይገኝም፡፡ እርሱንም በሌላ ስሙ ፍቅር ልንለው እንችላ
ለን፡፡ ስንቱ የእግዚአብሔር ሰው ፍቅርን ባለመለማመድ ሰላ
ሙንና ደስታውን ተነጥቆ እንደሚኖር መገመት አያስቸግር
ም፡፡

"እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም ፡- ጌታ ብላ እየጠራች
ው ታዘዘችለት፤እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ
ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ (የሣራ) ልጆቿ ናችሁ፡፡ እንዲ
ሁም እናንተ ባሎች ሆይ÷ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶ
ቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ ፀሎታችሁ እንዳይከ
ለከል..." (1ጴጥ3÷6-7) እግዚአብሔር ትዳርህን የማረፍያ ሥ
ፍራ ያድርግልህ፡፡ ለአንችም፡፡ የብዙዎችን÷በተለይም የሕ
ዝበ ክርስቲያንን ትዳር ለማወክ የተሰማሩ አጋንንት በጌታ
በኢየሱስ ቅዱስ ስም የታሰሩ ይሁኑ፡፡ አሜን፡፡

---

# ማስታወቅያ

ከአንባቢዎቻችን መሐከል የመጻሕ
ፍትና የቴፖች አገልግሎት ካለን
ማዘዝ እንደምትፈልጉ የጠየቃችሁ
ን ታስታውሳላችሁ፡፡ እኛም በዚህ
አኳያ ስንጸልይና ስንመክር ከቆየን
በኋላ አገልግሎቱን መጀመር የ
እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አ
ምነናል፡፡ በዚህም መሠረት ለክር
ስቲያን ተአንጾ የሚጠቅሙ መልእ
ክቶች ያዘሉ ቴፖችን ማዘጋጀትና
መሰብሰብ ጀምረናል፡፡

ፀጋ እንደበዛልንና ዝግጅታችን
በአግባቡ እንደ ተጠናቀቀ በዚሁ
መልእክት አማካኝነት እናስታው
ቃለን፡፡ ፀልዩልን፡፡

ጌታ ይባርካችሁ ፡፡



# መጽሐፍ ቅዱስ

## መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያስፈል
## ጋችሁ ማቅረብ ይቻለናል።

## ከዚህ በፊት እንዳስታወቅን
## ሁለት ዓይነት አጠራረዝ ያ
## ላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው
## ያለን። በስተ መጨረሻ ባለ
## ው አድራሻችን ጻፉልን።

*ከላይ የምታዩት ሥዕል ከምናስተዋውቀው መጽሐፍ የተወሰደ አይደለም።*

# እስፖንሰር

በኢትዮጵያና በኬንያ ወይም በሌሎች የአፍሪ
ካ ሐገሮች ያሉ ወገኖች ያውቃሉ? ለሚያውቋ
ቸው የአፍሪካ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ይህንን
መልእክት እስፖንሰር ማድረግ ይፈቅዳሉ? ለም
ሳሌ በኬንያ ላለ ሰው ይህንን መልእክት ለማድ
ረስ የፖስታ ዋጋ በየወሩ 0.80 ሣንቲም USA
በዓመት 9.60 ብቻ ነው። በጸሎት ያስቡበት።
ጌታ ይባርክዎ።

# የመንግሥተ ሰማይ ሚስጢር

መንግሥተ ሰማይ መግባት የማይመኝ ሰው የለም። በጣ
ም ደግ በመሆን፥የቤተክርስቲያን አባል በመሆን፥ብዙ
በመጾም ወይም ገዳም በመግባት የሚታገሉ አሉ። እነዚ
ህ መልካም ቢሆኑም በእግዚአብሔር ፊት ብቁ አያደር
ጉም። የሚከተለው መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከተመረመ
ረ በኋላ የተጠናቀረ እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ የገ
ለጸው መንግሥተ ሰማይ መግቢያ ሚስጢር ነው።

-- እግዚአብሔር ይወድሃል። "በእርሱ የሚያምን ሁ
ሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን
እንዲሁ ወዷልና።" (የዮሐንስ ወንጌል 3፥16)
-- ሰው ኃጢአተኛ ነው። "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል
ና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤" (ሮሜ 3፥23)
-- ኃጢአት ሞትን ያስከትላል። "የኃጢአት ዋጋ ሞት
ነውና" (ሮሜ 6፥23)
-- የኃጢአትህ ዕዳ ተከፍሏል። "ገና ደካሞች ሳለን ክ
ርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና"
(ሮሜ 5፥6)
-- ኢየሱስ በሞቱ ዕዳህን የከፈለልህ መሆኑን አምነህ
ተቀበል። "በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው
በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ
ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።" (የዮሐ/ወ 3፥36)
-- ዕምነትህን ተናገር። "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአ
ፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው
በልብህ ብታምን ትድናለህና" (ሮሜ 10፥9)

---

**ፀሎት**፦ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይህን ያነበብኩትን
መልዕክት፡በራስህ መንገድ ግለጽልኝ። መንግሥተ ሰማ
ይ ሚስጢር ሆኖብኝ እንዳልቀር የልቤን ዓይኖች አብራ
ልኝ። ስለ ስምህ ስትል። አሜን።

---

አቤቱ ፥ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይህንን ጽሑፍ ያነበበ
ሰው ሁሉ የመንግሥተ ሰማይ ተካፋይ መሆኑን ሳያውቅ
እንዳይሞትም፥ እንዳይሰንፍም አለምንሃለሁ። አሜን።
. ኢየሱስ ጌታ ነው
ጌታ ይባርክህ።

መላኩ ትዕዛዙ


አድራሻችን፦

GOD'S LOVE
PO BOX 6734
LEE'S SUMMIT MO 64086
E-MAIL mtizazu@hotmail.com
FAX 816 - 246 - 9395